# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# የጤና ኤክስቴንሽን አተገባበር መመሪያ (የተከለሰ)

DRAFT

ነሐሴ 2004 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

## ማውጫ


መግቢያ ..... 1
2.የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዓላማ ..... 4
2.1 ዋና ዓላማ ..... 4
2.2 ዝርዝር ዓላማዎች ..... 4
3. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መሰረታዊ ፍልስፍና ..... 4
4.ትርጓሜ ..... 5
5.የአፈፃፀም ስልቶች ..... 7
6. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበር ..... 8
7. የሞዴል ቤተሰብ የስልጠና ..... 10
8. ተግባርና ሀላፊነት ..... 12
8.1 የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር ተግባርና ሀላፊነት ..... 12
8.2 የክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ ተግባርና ሀላፊነት ..... 13
8.3 የዞን ጤና መመሪያ ተግባርና ኃላፊነት ..... 14
8.4 የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት ..... 14
8.5 የጤና ጣቢያ ተግባርና ኃላፊነት ..... 15
8.6 የቀበሌ አስተዳደር ተግባርና ሀላፊነት ..... 16
8.7 የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ ፕራክቲሽነሮች ተግባርና ኃላፊነት ..... 17
8.8 የልማት ቡድን ተግባርና ኃላፊነት ..... 17
8.9 የ1ለ5 ትስስር ተግባርና ኃላፊነት ..... 18
8.10 የቤተሰብ ተግባርና ኃላፊነት ..... 18
8.11 የት/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት ..... 19
8.12 የሴቶች አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት ..... 19
8.13 የአጋር ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት ..... 19
9. የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ ፕራክቲሽነሮች ዝውውር እና የአመት እረፍት ..... 20
9.1 የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ ፕራክቲሽነሮች ዝውውር ..... 20
9.2 የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ ፕራክቲሽነሮች የአመት እረፍት በተመለከተ ..... 22
10. ተከታታይነት ያለው የስራ ላይና የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ..... 23
11.የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የድጋፍና ክትትል ማዕቀፍ ..... 23
11.1 መደበኛ የጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት (HMIS) ..... 23
11.2 ድጋፋዊ ክትትልና ኢንስፔክሽን ..... 24
11.3 የአፈፃፀም ግምገማዎች ..... 25
12. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አደረጃጀት፣ ..... 26
አባሪ 1. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ፓኬጅ ይዘቶች ..... 27
አባሪ2. በጤና ኬላ ደረጃ ሊኖሩ የሚገባቸው መድኃኒቶችን የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶች ..... 28


DRAFT

## 1.መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ሰማንያ ከመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝብ በገጠር የሚኖርበት፣በወሊድና ከወሊድ ጋር በተያያዙ የጤና ችግሮች የእናቶችና የሕፃናት ሞት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰባትና የነበሩት የጤና ተቋማትም በአብዛኛው በከተሞች አካባቢ ብቻ የተከማቹበት ሁኔታ ነበር። በመሆኑም ችግሮቹን በመቅረፍ፣ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ለማስመዝገብ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተቀርፀው ሥራ ላይ ውለዋል። በዋናነት በሽታን በመከላከል ላይ ያተኮረው የጤና ፖሊስም ጤናማ ዜጋ የማፍራት ራዕይ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈጣንና ቀጣይ ዕድገት ለማምጣት በሚደረገው ጥረትም ጉልህ ስፍራ አለው። በመሆኑም የጤና ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ የጤና ልማት መርሃ ግብር ተቀርጾ በተለይ ከጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በርቀትና በተበታተነ አሰፋፈር የሚገኘውን የገጠሩን ማህበረሰብ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ በመተግበር ላይ ይገኛል። በዚህም መሰረት በእያንዳንዱ ቀበሌ በኣማካይ ለአምስት ሺ.ህ ህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ አንድ ጤና ኬላ በህብረተሰብ ተሳትፎ በመገንባት በሽታን በመከላከልና ጤናን በማበልፀግ ማህበረሰብና ቤተሰብ ተኮር መሠረታዊ የጤና አገልግሎቶች በመሰጠት ላይ ይገኛሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም ለአምስት የጤና ኬላዎች አንድ ጤና ጣቢያ በማደራጀት ለሃያ አምስት ሺ.ህ ሕዝብ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ ከየቀበሌው የተመለመሉ አስረኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ሴቶች በተመረጡ 16 የጤና ፓኬጆች ላይ ለአንድ ዓመት ስልጠና ከወሰዱ በኋላ በጤና ኬላ ሁለት ሁለት ሆነው እንዲመደቡ ተደርጓል። የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ዋና ተግባር በሽታን በመከላከል ጤናማነትን የማጎልበት መንፈስ እንዲሰፍን ማስቻል ነው። የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሴቶች ብቻ የሆኑበት ምክንያትም የእናቶችና የሕፃናትን ችግር የሚያውቁ፣በቤት አያያዝና በሕፃናት አስተዳደግ የተሻለ ክህሎትና ዘዴ ስላላቸው እንዲሁም አብዛኞቹ የጤና ችግሮች በእናቶችና ሕፃናት ላይ የሚከሰቱ በመሆናቸው ነው።

በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትግበራ ሂደት በርካታ ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን ከነዚህም ውጤቶች ከአምስት ዓመት በታች ሕፃናት ሞት በከፍተኛ መጠን መቀነሱ፣የመፀዳጃ ቤት ሽፋን ከፍተኛ ደረጃ መድረሱ፣የቤተሰብ እቅድና የህፃናት ክትባት ሽፋን እያደገ መምጣቱ እንዲሁም በወባና ኤች አይ ቪ ኤድስ ምክንያት የሚከሰተው ጉዳትና ሞት በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱ እንደ አብነት የሚጠቀሱ ናቸው። ይሁንና የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም በዘመቻ ስራ በመተግበሩና በማስፋት ስትራቴጂ ማዕቀፍ በጤና ልማት ሰራዊት ያልተመራና ያልተተገበረ በመሆኑ በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም።

ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በጤናው ሴክተር የተያዘውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካትና በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የተመዘገቡ ምርጥ ተሞክሮዎችን በአጭር ጊዜና ቀጣይነት ባለው መልኩ ወደ ሁሉም አካባቢዎችና ለሁሉም ህብረተሰብ በማዳረስ መሰረታዊ የጤና አገልግሎቶችን ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የጤና

DRAFT

ማስፋት ስትራቴጂ ተነድፎ በጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ቀደም የነበረውን የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበር መመሪያ በጤና ማስፋት ስትራቴጂና በጤና ልማት ሰራዊት መቃኘት አስፈላጊ በመሆኑ መመሪያው ተከልሷል፡፡ በዚህ መመሪያ የፕሮግራሙ ዓላማዎች፣የአፈፃፀም ስልቶች አደረጃጀት፣ተግባርና ሀላፊነት እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ተካተዋል፡፡ መመሪያው የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣በየደረጃው ያሉ የጤናና የመስተዳደር አካላት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲጠቀሙበት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

# 2.የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዓላማ

## 2.1 ዋና ዓላማ

የህብረተሰቡን ጤና በማበልፀግና በሽታን በመከላከል ተግባር ላይ ያተኮረ፣ቤተሰብንና ህብረተሰብን ማዕከል ያደረገ የጤና አገልግሎት በፍትሐዊነት ለህዝቡ ማዳረስ ነው፡፡

## 2.2 ዝርዝር ዓላማዎች

- የጤና ልማት ሰራዊት አደረጃጀትን በመጠቀም ህብረተሰቡ በራሱ የጤና ጉዳይ ላይ ውሳኔ በመስጠት የራሱን ጤና በራሱ እንዲጠብቅ ማስቻል
- የህብረተሰቡን ንቃተ ጤና በማሳደግ ጤናማ አስተሳሰብና ባህሪ በመፍጠር የጤና ማበልፀግና በሽታን የመከላከል ተግባራትን ማጎልበት
- በእናቶችና ህፃናት ጤና ላይ የበለጠ ትኩረት በመስጠት የእናቶችና የህፃናትን ጤናን ማበልፀግ
- ጥራቱን የጠበቀ መሰረታዊ የጤና አገልግሎትን ሙሉ በሙሉ ማዳረስ
- ህብረተሰቡን መሰረት ያደረገ የጤና አገልግሎት የቅብብሎሽ ስርዓት ማዳበር

# 3. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መሰረታዊ ፍልስፍና

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መሰረታዊ ፍልስፍና በሰለጠኑ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራክቲሽነሮች አማካኝነት የጤና መልዕክቶችንና ተግባራትን ወደ እያንዳንዱ ቤትና ቤተሰብ በማድረስ የህብረተሰቡን ንቃተ ጤና በማሳደግ አዎንታዊ አመለካከት ማምጣትና እንደ ግብርና ምርት ሁሉ የጤና ምርት እንዲያመርት ማስቻል ነው፡፡

DRAFT

## 4.ትርጓሜ

### 4.1 የጤና አክስቴንሽን ፐሮግራም

የጤና አክስቴንሽን ፐሮግራም በፓኬጅ መልክ የተዘጋጀ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ዋነኛ አካል ሲሆን ቤተሰብንና ማህበረሰብን ማዕከል በማድረግ የህብረተሰቡን ጤና ማሳደግ የሚያስችል እውቀትና ክህሎት በመፍጠርና አቅምን በማጎልበት ላይ የሚያተኩር በሰለጠኑ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራክቲሽነሮችና በማህበረሰብ የሚተገበር፣ ጤናን በማበልፀግና በሽታን በመከላከል ህብረተሰቡ የራሱን ጤና የሚወስንበትና እርምጃ የሚወስድበት የጤና አገልግሎት ድልድይ ነው፡፡

### 4.2 የቤተሰብ ፓኬጅ

የቤተሰብ ፓኬጅ ማለት አንድ ቤተሰብ በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራክቲሽነሮችና በ1ለ5 ትስስር መሪዎች ስልጠናና ቀጣይነት ያለው ድጋፍና ክትትል አማካኝነት የሚመለከተውን ሁሉንም የጤና ፓኬጆች በመተግበር ጤናን የማበልፀግና በሽታን የመከላከል ተግባራትን በመፈፀም ጤናውን እንዲያመርትና እንዲያባዛ የሚያስችል ስልት ነው፡፡

### 4.3 የማህበረሰብ ፓኬጅ

የማህበረሰብ ፓኬጅ ማለት በአንድ ቀበሌ የሚገኙትን የልማት ቡድኖች፣የተለምዶ ማህበራት (ማለትም ዕድር፣ ዕቁብ ወዘተ)፣የእምነት ተቋማት፣የገበያ ቦታዎች፣የመንግስት አወቃቀር(ለምሳሌ፡- ት/ቤቶች፣የግብርና ልማት ጣቢያዎች) እና የብዙኃን ማህበራትን (የሴቶች፣የወጣቶች፣የአርሶ አደር) በመጠቀም እንዲሁም በውሎ ገብ የጤና አገልግሎቶችን በመስጠት የቀበሌው ህብረተሰብ በአጠቃላይ በጤና ላይ ያለውን ግንዘቤ አዳብሮ በሽታን መከላከልን በባለቤትነት እንዲመራ እንዲሁም የአገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችል ስልት ነው፡፡

### 4.4 የጤና ማስፋት ስትራቴጂ

የጤና ማስፋት ስትራቴጂ ማለት በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የተመዘገቡ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር በአንድ ጊዜ ለሁሉም ቤተሰቦች የምናዳርስበት፤ በዚህ ሂደትም ማነቆዎችን የምንለይበትና የምንፈታበት እንዲሁም የማስፈፀም አቅማችንን በመገንባት ሁሉም ቤተሰቦች የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን ቀጣይነት ባለው መልኩ በመተግበር ጤናቸውን እንዲያመርቱ የሚያስችል ስልት ነው፡፡

### 4.5 የጤና ልማት ሰራዊት

የጤና ልማት ሠራዊት ማለት ከህብረተሰቡ ጀምሮ እስከ ላይኛው አመራር ድረስ ማለትም ህዝቡ፣ ባለሙያውና አመራሩ በአንድ የጋራ አላማ ዙሪያ እንደ አንድ ተሳስሮ በተደራጀ ሁኔታ የጤና የማስፋት ስትራቴጂውን ስራ ለመተግበር የሚያስችል የማስፈጸም አቅም ማለት ነው፡፡

DRAFT

### 4.6 የልማት ቡድን

የልማት ቡድን ማለት በቀበሌ ውስጥ የተዋቀረ በአማካይ ከ20-30 ቤተሰቦችን በስሩ በማቀፍና በ1ለ5 በማደራጀት የልማት ስራዎችን የሚሰራ በየጊዜው ራሱን እየገመገመ የልምድ ልውውጥ የሚያደርግ አደረጃጀት ነው፡፡

### 4.7 የ1ለ5 ትስስር

የ1ለ5 ትስስር ማለት በአንድ ጎጥ/መንደር ውስጥ በመኖሪያ ቤታቸው የሚቀራረቡ ስድስት ቤተሰቦች በአንድ ላይ በመደራጀትና ከመካከላቸው በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ አፈፃፀም በተሻለ ቤተሰብ እየተመሩ ሁሉም በትስስሩ ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች የሚመለከታቸውን ሁሉንም የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች እንዲተገብሩ የሚያስችል አደረጃጀት ነው፡፡

### 4.8 ግንባር ቀደም ቤተሰብ

ግንባር ቀደም ቤተሰብ ማለት ቤተሰቡን የሚመለከቱ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን ሙሉ በሙሉ የተገበረ ወይም ለመተግበር የተዘጋጀ እንዲሁም በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ስልጠና ወስዶ በራሱ በመተግበር በፍቃደኝነት ሌሎችን ቤተሰቦች የሚደግፍ ማለት ነው፡፡

### 4.9 ሞዴል ቤተሰብ

ሞዴል ቤተሰብ ማለት በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራክቲሽነሮችና በ1ለ5 ትስስር መሪ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ቤተሰቡን የሚመለከቱ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን ሙሉ በሙሉ የተገበረ ማለት ነው፡፡

### 4.10 የጤና ጣቢያና ጤና ኬላ ትስስር

የጤና ጣቢያና ጤና ኬላ ትስስር ማለት ጤና ጣቢያንና በዙሪያው ያሉትን በአማካይ አምስት ጤና ኬላዎች ለአንድ ዓላማ እንደ አንድ መሰረታዊ ጤና ክብካቤ አሃድ አቀናጅቶ ለመምራትና ለማስተባበር የሚያስችል አሰራር ነው፡፡

DRAFT

## 5.የአፈፃፀም ስልቶች

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን በተሳካና ውጤታማ በሆነ ምልኩ ተግባራዊ ለማድረግ በዋናነት የሚከተሉት ስልቶች በስራ ላይ ይውላሉ፡፡

### 5.1 የጤና ልማት ሰራዊት መገንባትና መጠቀም

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተግባራዊነት በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራክቲሽነሮች ጥረት ብቻ የሚሳካ ባለመሆኑ ለተግባራዊነቱ የጤና ልማት ሰራዊት በመገንባት ሕብረተሰቡን በልማት ቡድንና በ1ለ5 በማደራጀት የጤና ልማት ስራዎችን ማከናወን የግድ ነው፡፡ በመሆኑም የጤና ልማት ሰራዊት መገንባት ህብረተሰቡ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን በባለቤትነትና እንዲይዝና ጤናውን እንዲያመርት ያስችላል፣በፕሮግራሙ የተያዙ ግቦችንም በተሻለ ፍጥነትና ጥራ ማሳካት ይቻላል፡፡

### 5.2 የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድን ማጠናከር

የጤናኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ጤና ጣቢያና ጤና ኬላዎች እንደ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ ማደራጀት ይገባል፡፡ በዚህም የፕሮግራሙን ፓኬጆች ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ሳይቆራረጡ በወቅቱ ለማቅረብ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች ወደ ጤና ኬላ ወርደው ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች አቅማቸውን ለመገንባትና የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን የቅብብሎሽ ስርዓት ለማጠናከር ይረዳል፡፡

### 5.3 ዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ

ግብ ጥሎ መስራት የእቅድ አፈፃፀሙ ከየት ተነስቶ የት ለመድረስና ምን ውጤት መቼ ማግኘት እንደሚቻል በቀላሉ ለመረዳትና ለመከታተል እንዲሁም በእቅድ አፈፃፀም ሂደት የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን በየደረጃው ለመለየትና ለመፍታት የሚያስችል ስልት ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ የእቅድ ክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ በማዘጋጀት የሚያስፈልገውን ግብ በወቅቱና በሚጠበቀው ደረጃ ማከናወን ይገባል፡፡ በዚህ ሂደት በየደረጃው የተመዘገቡ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋት የፕሮግራሙን ስኬታማነት በዘላቂነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

### 5.4 ተከታታይነት ያለው የስራ ላይና የሙያ ማሻሻያ ስልጠና መስጠት

የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን በብቃት እንዲፈፅሙና ለህብረተሰቡ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ተከታታይነት ያለው የስራ ላይ ስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን በተቀናጀ የማጠናከሪያ ስልጠና ወቅቱን ጠብቆ ማሰልጠን ይገባል፡፡

### 5.5 ቅንጅታዊ አሠራርን ማስፈን

የጤና ጉዳይ በአብዛኛው ከጤናው ሴክተር ውጭ ያሉ የሴክተር መስሪያ ቤቶችንና የልማት አጋሮችን ድጋፍና አስተዋጽኦ የሚጠይቅ ነው፡፡ በተለይም በቀበሌ ደረጃ የሚኖረው ቅንጅታዊ አሠራር አስፈላጊነቱ እጅግ የላቀ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ደረጃ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት መረጃን በመለዋወጥና በመጋራት፣የልምድ ልውውጥ መድረክን በመፍጠር፣የጋራ ዓላማን ለማሳካት ሀብትን በአግባቡና በቁጠባ በመጠቀም፣በእቅድ በትግበራ በክትትልና ግምገማ በማሳተፍ የቀበሌውን የጤና ልማት ግቦች ለማሳካት ቅንጅታዊ አሠራርን ማስፈን ተገቢ ነው፡፡

DRAFT

## 6. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አተገባበር

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ፓኬጆችን ለህብረተሰቡ ለማድረስ በቤት ለቤት፣በማህበረሰብ፣ በጤና ኬላ ደረጃና በማህበራዊ ተቋማት አገልግሎቶቹ ይሰጣሉ፡፡

### 6.1 በቤተሰብ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት

የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራክቲሽነሮች ግማሽ ያህል የስራ ጊዜያቸውን በቤትለቤትና በማህበረሰብ ደረጃና ግማሹን ደግሞ በጤና ኬላ ደረጃ ለሚሰጡ አገልግሎቶች መመደብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ሲባል አንደኛዋ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ/ፕራክቲሽነር በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ የሚሰጡ አግልግሎቶችን ስትሰጥ ሌላኛዋ በጤና ኬላ አገልግሎት ትሰጣለች፡፡ሁለቱ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራክቲሽነሮች በዚህ መልኩ ተፈራርቀው ሲሰሩ የጤና ኬላው ሳምንቱን ሙሉ ክፍት ይሆናል ማለት ነው፡፡

**በቤተሰብ ደረጃ በሚከናወኑ ተግባራት ትኩረት የሚሰጣቸው አከላት**

- ነፍሰጡር ሴቶች፣የወለዱ እናቶች፣ጨቅላ ህፃናት ያሉባቸው ቤተሰቦች
- በከባድ ህመም የታመሙ የቤተሰብ አባላት ያሉበት ቤተሰቦች
- በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ቤተሰቦች

**በቤተሰብ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት**

- የቤሰተብ ምጣኔ፣የቅድመወሊድ ክትትል፣ የድህረ ወሊድ ክትትልና የክትባት አገልግሎት መስጠት
- በጉብኝት ወቅት መሰረታዊ የህክምና አገልግሎት መስጠት
- የ1ለ5 ትስስር መሪዎች ያከናወኑትን ተግባራት መከታተል፣መደገፍና መገምገም እንዲሁም ጥራቱን ማረጋገጥና ግልፅነቱን ማየት
- ዝቅተኛ የፓኬጅ አፈፃፀም ያላቸውን ቤተሰቦች ትኩረት በማድረግ በሚመለከታቸው በሁሉም የጤና ፓኬጆች ላይ ድጋፍ ማድረግ
- የጤና ትምህርትን መስጠት
- ሞዴል ቤተሰቦች ወደ ኋላ እንዳይመለሱ መከታተልና ማበረታታት

### 6.2 በማህበረሰብ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት

በማህበረሰብ ደረጃ የሚገኙ የልማት ቡድኖችን፣የብዙኃን ማህበራትን (የሴቶች፣የወጣቶች፣የአርሶ አደር)፣የተለምዶ ማህበራት (ማለትም ዕድር፣ ዕቁብ ወዘተ)፣የእምነት ተቋማት፣የገበያ ቦታዎች፣የመንግስት አወቃቀር(ለምሳሌ፡- የግብርና ልማት ጣቢያዎች) በመጠቀም የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡

**በማህበረሰብ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፡፡**

- በጤና ፓኬጆች ላይ ትምህርት መስጠትና የጤና አገልግሎት መስጠት፡፡
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ቀበሌውን በጎጥ በመከፋፈል በውሎ ገብ የጤና አገልግሎቶችን መስጠት
- የ1ለ5 ትስስሮችንና የልማት ቡድኖችን ማደራጀት፣መከታተል፣መደገፍና መገምገም

DRAFT

- ከልማት ቡዱኖች ጋር በአስራ አምስት ቀን አንድ ጊዜ ሳይቆራረጥ ስብሰባ ማካሄድና የስራ አፈፃፀማቸውን መገምገም

## 6.3 በወጣት ማዕከላትና በትምህርት ቤት የሚከናወኑ ተግባራት

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን በቀበሌ ከመተግበር አኳያ ት/ቤቶችና የወጣት ማዕከላት ተቋማትን መጠቀም ከፍተኛ ሚና አለው።

**በት/ቤትና በወጣት ማዕከላት የሚከናወኑ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።**

- በወጣት ማዕከላት በጤና ፓኬጆች ላይ ትምህርት መስጠትና የጤና አገልግሎት መስጠት
- የጤና ፓኬጁን በት/ቤቶች በሞዴልነት መተግበርና ተማሪዎችን ማስተማር
- ተማዎችን ማደራጀትና ስልጠና መስጠት ወይም የትምህርት ቤት የተለያዩ ክለቦችን መጠቀም

## 6.4 በጤና ኬላ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት

**በጤና ኬላ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።**

- የተቀናጀ የማህበረሰብ አቀፍ የህፃናት ህክምና መስጠት
- የክትባት ቅዝቃዜ ሰንሰለት የሙቀት መጠንን መመዝገብና መቆጣጠር
- የክትባት አገልግሎት መስጠት
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስጠት
- የቅድመ ወሊድ ወሊድና ድህረ ወሊድ አገልግሎት መስጠት
- የህፃናት ነፍሰጡሮችና የሚያጠቡ እናቶች የስነ ምግብ እጥረት ልየታና የምክር አገልግሎት መስጠት
- በየወሩ በቀበሌው የሚገኙ ነፍሰጡሮችን ማወያየት
- የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ መስጠት
- የወባ ምርመራ አር ዲ ቲን በመጠቀም መመርመር በውጤቱ መሰረት ህክምና አገልግሎት መስጠት
- የኤች አይ ቪ ምክርና ምርመራ አገልግሎት መስጠት (የደረጃ አራት ስልጠናን ባጠናቀቁ የጤና ኤክስቴንሽን ፕራክቲሽነሮች የሚሰራ)
- የማህበረሰብ አቀፍ የቲቢ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት መስጠት
- የቴትራሳይክሊን ቅባትን በመጠቀም የትራኮማ በሽታን ማከምና ስለ ፊት መታጠብ ማስተማር
- የእከክ በሽታን ህክምና መስጠት
- ከጤና ኬላ አቅም በላይ የሆኑ የጤና አገልግሎቶችን ወደ ጤና ጣቢያ መላክ
- በጤና ኬላ ሰርቶ ማሳያዎችን በማዘጋጀትና በመጠቀም የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት
- የተከናወኑ ስራዎችን መመዝገብ፣ፋይል ማደራጀት፣መረጃን ማጠናቀርና ሪፖርት ማቅረብ

DRAFT

- አስፈላጊ መረጃዎችን በግራፍና በቻርት በመስራት ግድግዳ ላይ በመለጠፍ ውቅታዊ ማድረግ

## 7. የሞዴል ቤተሰብ የስልጠና

የሞዴል ቤተሰብ ስልጠና በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ላይ በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራክትሽነሮች ና በ1ለ5 ትስስር አማካኝነት የሚሰጥ ስልጠና ነው፡፡

DRAFT

### 7.1 የሞዴል ቤተሰብ የስልጠና ሂደት

በቀበሌ ደረጃ ከ150 እስከ 200 የሚደርሱ በፓኬጅ አፈፃፀማቸው መሰረት ደረጃ ተሰጥቷቸው የ1ለ5 መሪ ተብለው በልማት ቡድን የተመረጡ ሴቶች በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራክቲሽነሮችና በጤና ጣቢያ ባለሙያዎች አማካኝነት ለ15 ቀናት በቀን ለ4 ሰዓት በድምሩ ለ60 ሰዓታት የክህሎት ስልጠና ይወስዳሉ፤ በስልጠናው ጊዜና ከዚያም በኋላ በተግባር ፓኬጆቹን በቤታቸው ይተገብራሉ ፓኬጆቹን ሲያሟሉ በሞዴልነት ይመረቃሉ፡፡ የ1ለ5 ትስስር መሪዎች በስራቸው ከሚገኙ ቤተሰቦች ጋር ለሁለት ቀናት በፓኬጆቹ አተገባበር ዙሪያ ውይይት በማድረግ የትስስራቸውንና የየግል እቅዳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ የፓኬጆች ትግበራን የጊዜ ሰሌዳ ያስቀምጣሉ፤ በተቀመጠው እቅድና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የ1ለ5 መሪዎች ሳይቆራረጥ ድጋፍና ክትትል በማደረግ ሁሉንም ቤተሰቦች ቢበዛ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ የሚመለከታቸውን ሁሉንም ፓኬጆች በመፈፀም ሞዴል ሆነው እንዲመረቁ ያደርጋሉ፡፡ ሞዴል ሆነው የተመረቁ ቤተሰቦች ወደ ኋላ እንዳይመለሱ በጤና ኤክስቴንሽን  ሰራተኞች በመታገዝ የ1ለ5 መሪዎች ቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

### 7.2 የሞዴል ቤተሰብ ምረቃ መስፈርቶች

አንድ ቤተሰብ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ሞዴል ሆኖ ለመመረቅ የሚከተሉትን መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

**የእናቶችና ህፃናት ጤና**

- ከአንድ አመት ባታች የሆኑት ህፃናት ሁሉንም የክትባት አይነት ካስከተቡ
- አዲስ የተወለዱ ህፃናት እስከ ስድስት ወር ለምንም ተጨማሪ ምግብ የእናት ጡት ብቻ ከጠቡ
- ህፃናትን  በአግባቡ ከመገቡ
- ከሁለት አመት በታች ያሉ ህፃናት የእድገት ክትትል ካደረጉ
- ቤት ውስጥ ያሉ ከ15 በላይ የሆኑ ሴቶች ክትባት ከወሰዱ
- የቤተሰብ እቅድ እውቀት ያሻሻሉ ወይም ተጠቃሚ ከሆኑ
- የታመሙ እናቶችና ህፃናት በቶሎ ወደ ህክምና መውሰድ ከተለመደ

- ተቅማጥ ለያዘው ህጣን ፈሳሽ ምግቦችን እና ኦ አር ኤስ መስጠት ከተለመደ
- ጎጂ ልማዶች ስወገዱ ከሆነ
- ነፍሰ ጡር ሴት ቅደመ ወሊድ አገልግሎት ከሶስት እስከ አረት ጊዜ ካደረገች
- የወሊድ አገልግሎት በሰለጠነ ባለሙያ ያገኘችና የድህረ ወሊድ አገልግሎት ከወሊድ በኃለ ሁለት ጊዜ አድርጋ ከሆነ

**ወባን በተመለከተ**

- የመኝታ  አጎበር ካላቸው አዘውትረው  ከተጠቀሙ
- የወባ ህመም ሲከሰት በፍጥነት ወደ ጤና ተቋም  የሚሄዱ ከሆነና የሚሰጣቸውን መድሃኒት በአግባቡ የሚጠቀሙ ከሆነ
- የወባ መከላከል የአከባቢ ቁጥጥር ስራዎች ላይ ከተሳተፉ
- የፀረ ወባ ኬሚካል ቤታቸውን ካሰረጩ

**የግልና የአከባቢ ንፅህና**

- በመፀዳጀ ቤት አጠገብ የእጅ መታጠቢያ በማዘጋጀት ከተፀዳዱ በኃላ እጅን በአመድ ወይም በሳሙና መታጠብ
- የመፀዳጃ ት መገንባትና በአግባቡ ሁሉም የቤተሰብ አባላት አዝትው መጠቀም
- ቤትን በንጽህና መያዝ
- የደረቅ ቆሻሻማጠራቀሚያ መጠቀም ወይም ለኮምፖስት መጠቀም
- የፍሳሽማረጊያ ጉድድ ተዘጋጅቶ በጥቅም ላይ ከዋለ
- የመመገቢያ እቃዎች ንፅህናቸው ተጠብቆ በትክክል ከተደረደሩ
- መክደኛ ያለው በቀላሉ ሊታጠብ የሚችል ለስላሳ የምግብ እቃ በጥቅም ላይ ከዋላ
- ምግብ ሲዘጋጅና ሲሰራ በንፅህና መያዝ ከተለመደ
- ህፃናትን ከተፀዳዱ በኃላ እጅን መታጠብ
- ፍትንና እጅን ሁል ጊዜ መታጠብ
- በሳምንት ቢያንስ አንድ ጊዜ ገላን መታጠብ
- ፀጉርና ጥፍርን በአጭር መያዝ
- የገላና የልብስ ተባዮችን ያስወገዱ
- የአከባቢ ንፅህና በትክክል ከተያዘ
- የተለየ ማብሰያ ቤት ያዘጋጀ
- የሰውና የእንስሳት መኖሪያ ቤት ከለዩ
- ቤትን በየጊዜው በመለቅለቅ ሙጀሌንና ሌሎች ተባዮችን መስወገድ ነገር ግን በፀረ ወባ ኬሚካል የተረጨን ግድግዳ እስከ ስድስት ወራት ያልተለቀለቀ

**የውሃ አያያዝና አጠቃቀም**

- የውሃ መቅጃን ለይቶ ማስቀመጥ
- ከምንጭ አስተማማኝ ያልሆነ የመጠጥ አፍልቶ ወይም አጣርቶ መጠቀም
- የቤት ውስጥ ውሃ ፍጆታ ከጨመረ

DRAFT

**ኤች አይ ቪ/ኤድስና ቲቢ**

- ስለመተላለፊያና መከላከያ ዘዴዎች በቂ ግንዛቤ ካላቸው
- በማህበረሰብ ውይይት ተሳታፊ ከሆኑ
- መድሎና ማግለል የማያደርጉ ከሆነ
- ሁለት ሳምንትና ከዚያ በላይ የቆየ ሳል ካላቸው ወደ ጤና ተቋም ለምርመራ የሚሄዱ ከሆነ
- የሚሰጣቸውን የቲቢ ህክምና በአግባቡ ወስደው የሚጨርሱ ከሆነ

# 8. ተግባርና ሀላፊነት

## 8.1 የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር ተግባርና ሀላፊነት

**ቁልፍ ተግባር**

- የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታን ቁልፍ ተግባሩ አድርጎ መንቀሳቀስ፣

**አበይት ተግባራት**

- የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድን ማጠናከር፣
- መመሪያዎችንና ለፕሮግራሙ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ማዘጋጀት ተፈፃሚነታቸውንም መከታተል፣
- ከፌዴራል መንግስት ከሴክተር መስሪያ ቤቶች ከክልል ምክር ቤቶች ከጤና ቢሮዎችና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መሳካት በጋራ መስራት፣
- በየክልሉ ለተዋቀሩ ኮማንድ ፖስቶችን መደገፍ፣ መከታተል፣ የመረጃ ልውውጥ ማድረግና በቅንጅት መስራት፣
- በየዓመቱ ሁሉንም ክልሎችና አጋር ድርጅቶችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ፤ በዚህም በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም የተሻለ ደረጃ ላላቸውና የላቀ አስተዋፅዖ ላበረከቱ አካላት እውቅናና ማበረታቻ መስጠት፣
- የድጋፍዊ ክትትል ስራዎችን ማከናወን፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የስራ ላይ ስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ትምህርት የሚያገኙበትን ስርዓት መዘርጋት፤ ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- የፕሮግራሙን አፈጻጸም ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ማካሄድ/ማስተባበር፣
- ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ማዘጋጀት፣
- ወጥነት ያላቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ ሪፖርት ማቅረቢያ የክትትልና የግምገማ ቅጾችን ማዘጋጀትና ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣
- የጤና አጠባበቅ መርጃ መሳሪያዎችን፣ የስልጠና ማኑዋሎችንና የማጣቀሻ መጽሐፎችን ማዘጋጀት፣

DRAFT

## 8.2 የክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ ተግባርና ሀላፊነት

**ቁልፍ ተግባር**

- የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታን ቁልፍ ተግባሩ አድርጎ ይንቀሳቀሳል

**አበይት ተግባራት**

- የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድን ማጠናከር፣
- በክልሉ የተዋቀሩ ኮማንድ ፖስቶችን መደገፍ፣ መከታተል፣ የመረጃ ልውውጥ ማድረግና በቅንጅት መስራት፣
- በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን መሰረት በማድረግ እንደየክልሉ ነባራዊ ሁኔታ በማሻሻል ተፈፃሚነታቸውን መከታተል፣
- ከክልሉ መንግስት፣ ከሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ ከዞን፣ ከወረዳና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መሳካት በጋራ መስራት፣
- ለዞን ጤና መምሪያ የቴክኒክና አስተዳደራዊ ድጋፍ መስጠት፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በክልሉና ከክልሉ ውጭ የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፋ ማድረግ፣
- በየስድስት ወሩ በየደረጃው ያሉ አካላትንና አጋሮችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ በማዘጋጀት በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላላቸው አካላት እውቅናና ማበረታቻ መስጠት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የስራ ላይ ስልጠና የሙያ ማሻሻያ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ፤ አፈፃፀሙን መከታተል፣
- በተለያዩ ምክንያቶች ስራቸውን በለቀቁ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ምትክ የማሟሚያ ስልጠና ማካሄድ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈጻጸም ላይ ጥናቶችን ማካሄድ/መደገፍ፣
- የድጋፍዊ ክትትል ስራዎችን ማከናወን፣
- የጤና አጠባበቅ መርጃ መሳሪያዎችንና የማጣቀሻ መጽሐፎችን ማዘጋጀት፣
- ለፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየወቅቱ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ፣

DRAFT

## 8.3 የዞን ጤና መመሪያ ተግባርና ኃላፊነት

**ቁልፍ ተግባር**

- የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታን ቁልፍ ተግባሩ አድርጎ መንቀሳቀስ፣

**አበይት ተግባራት**

- በዞንና በወረዳ የተዋቀሩ ኮማንድ ፖስቶችን መደገፍ፤መከታተል፤ የመረጃ ልውውጥ ማድረግና በቅንጅት መስራት፣
- የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሀድን መደገፍ፤መከታተል፤
- በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ርና በክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ የሚወጡ መመሪያዎችንና ደንቦችን ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ከዞን መስተዳደር ምክር ቤት፣ ከሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ ከወረዳና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መሳካት በጋራ መስራት፣
- ለወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ መስጠት፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፋ ማድረግ፣
- በየሩብ አመቱ በየደረጃው ያሉ አካላትንና አጋሮችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ በማዘጋጀት በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላላቸው አካላት እውቅናና ማበረታቻ መስጠት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የስራ ላይ ስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ፤ አፈፃፀሙን መከታተል፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰልጣኞችን የማሟያ ምልመላ ማገዝና ማስተባበር፣
- የድጋፍዊ ክትትል ስራዎችን ማከናወን፣
- የጤና አጠባበቅ መርጃ መሳሪያዎችንና የማጣቀሻ መጽሐፎችን ማዘጋጀት፣
- የጤና ኬላና የጤና ኤክስቴንሽን መኖሪያ ቤት ግንባታና ጥገና ሥራዎችን መከታተል፣
- ለክልል ጤና ቢሮዎች በየወቅቱ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ፣

## 8.4 የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

**ቁልፍ ተግባር**

- የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታን ቁልፍ ተግባሩ አድርጎ መንቀሳቀስ፤ወረዳውን በተደራጀ የህዝብ ንቅናቄ መምራት፣

DRAFT

**አበይት ተግባራት**

- በወረዳና በቀበሌ የተዋቀሩ ኮማንድ ፖስቶችን መደገፍ፤መከታተል፤ የመረጃ ልውውጥ ማድረግና በቅንጅት መስራት፣
- በወረዳው የሚገኙ ሁሉም ጤና ጣቢያዎችና ጤና ኬላዎች በመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሃድ መርህ መሰረት ማስተሳሰር፤መደገፍ፤መከታተል፣
- በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ርና በክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ የሚወጡ መመሪያዎችንና ደንቦችን ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ከወረዳ መስተዳደር ምክር ቤት፣ ከሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ ከአጋር ድርጅቶች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መሳካት በጋራ መስራት፤
- ለጤና ጣቢያዎች የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ መስጠት፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፋ ማድረግ፣
- በየሩብ አመቱ በየደረጃው ያሉ አካላትንና አጋሮችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ በማዘጋጀት በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላላቸው አካላት እውቅናና ማበረታቻ መስጠት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የስራ ላይ ስልጠና መስጠት፤የሙያ ማሻሻያ ትምህርት እንዲያገኙ ምልመላ ማድረግ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰልጣኞችን የማሟያ ምልመላ ማካሄድ፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ኢንስፔክሽን/ድጋፍና ክትትል ማካሄድ፤ግብረ መልስ መስጠት፣
- ለክልል ጤና ጥበቃ ቢሮና ለዞን ጤና መምሪያ በየወቅቱ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ፣
- የጤና ኬላና የጤና ኤክስቴንሽን መኖሪያ ቤት ግንባታና ጥገና ሥራዎችን ከቀበሌው አስተዳደር ጋር በመሆን ማከናወን/ማስተባበር፤
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ኢንስፔክሽን/ድጋፍና ክትትል ማካሄድ፣ ግብረ መልስ መስጠት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን ቅጥር መፈፀም፤የጎደለትንም ማሟላት፤

## 8.5 የጤና ጣቢያ ተግባርና ኃላፊነት

**ቁልፍ ተግባር**

- የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታን ቁልፍ ተግባሩ አድርጎ መንቀሳቀስ፤በስሩ ያሉ ቀበሌዎችን በተደራጀ የህዝብ ንቅናቄ መምራት፣
- በስሩ ላሉ የጤና ኬላዎች መደግፍ፤መከታተልና መገምገም፣



DRAFT

**አበይት ተግባራት**

- የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሀድ ዕቅድን ማዘጋጀት፣
- በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት በአመለካከት፣ በክህሎትና በግብዓት አቅርቦት ያሉትን ማነቆዎች በመለየት የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማስፈፀም፣
- በጤና ጣቢያው ስራ ባሉ ቀበሌዎች ያሉ የልማት ቡድንና የ1ለ5 ትስስሮችን እና ሌሎች ጤናና ጤና ነክ መረጃዎችን መሰብሰብ፤መተንተን፤
- ለጤና ኬላዎች የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ መስጠት፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር እንዲሰፉ ማድረግ፣
- በየወሩ በስሩ ካሉ ጤና ኬላዎች ጋር የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማካሄድ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የስራ ላይ ስልጠና መስጠት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራክቲሽነሮች በጤና ኬላ በማይኖሩበት ወቅት አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ ሌሎች ባለሙያዎችን በጊዚያዊነት መድቦ ማሰራት፣
- በጤና ጣቢያ የሚገኙ ባለሙያዎች ጤና ኬላዎችን በመከፋፈል የጤና ልማት ሰራዊት ስራዎችን ቀበሌ ወርደው እንዲደግፉ ማድረግ፣
- የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ በመዘርጋት ተግባራቱን መከታተል፣
- ለወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በየወቅቱ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ፣

## 8.6 የቀበሌ አስተዳደር ተግባርና ሀላፊነት

**ቁልፍ ተግባር**

- የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታን ቁልፍ አጀንዳ አድርጎ መንቀሳቀስ፤

**አበይት ተግባራት**

- የቀበሌውን የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ለመከታተልና ለመደገፍ ኮማንድ ፖስት ማቋቋም፣
- የልማት ቡድኖችንና የ1ለ5 ትስስሮችን በቋሚነት መሰብሰብ፣መከታተል፣መደገፍና መገምገም፤
- በቀበሌው ያሉ የልማት ቡድንና የ1ለ5 ትስስሮችን መረጃዎችን መሰብሰብ፤መተንተን፤
- ማህበረሰቡን በማስተባበር ደረጃውን የጠበቀ የጤና ኬላ ግንባታና እድሳት እንዲሁም የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች መኖሪያ ቤትና የሞዴል ሰርቶ ማሳያ ግንባታዎችን ማከናወን፤
- የቀበሌውን የጤና ልማት ስራ በዋነኛነት መምራት፤የህብረተሰብ ንቅናቄ መፍጠር፤ ማስተባበር፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ/ፕራክቲሽነር በቀበሌው ውላ አድራ መስራቷን መከታተል፣

DRAFT

## 8.7 የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ ፕራክቲሽነሮች ተግባርና ኃላፊነት

**ቁልፍ ተግባር**

- የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታን ቁልፍ ስራቸው አድርገው መንቀሳቀስ፣

**አበይት ተግባራት**

- ከጤና ጣቢያ፣ ቀበሌ አስተዳደርና ሌሎች አካላት ጋር በመሆን ዕቅድ ማዘጋጀት፣ መተግበር፣ አፈፃፀሙን በጋራ መገምገም፣
- የልማት ቡድኖችንና የ1ለ5 ትስስሮችን በቋሚነት መሰባሰብ፣መከታተል፣መደገፍና መገምገም፤
- የቀበሌውን የጤና ዕቅድ  በልማት ቡድን በ1ለ5ና በቤተሰብ ደረጃ መከፋፈሉን ማረጋገጥ፣
- አጠቃላይ የቀበሌውን ጤናና ጤና ነክ መረጃዎችን ቤተሰብ ጤና ማኅደር በመሰባሰብ መተንተንና ማጠናቀር እንዲሁም የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለጤና ጣቢያ መላክ፤
- ጤና ኬላውን በየቀኑ ክፍት በማድረግ በጤና ኬላ የሚሰጡ አገልግሎቶችን መስጠት፣
- በመደበኛነት የቤት ለቤት ጉብኝት ማድረግ እንዲሁም በውሎ ገብ የሚሰሩ ሥራዎችን ማከናወን፤
- ለፕሮግራሙ የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችን፣ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችንና ሌሎች ግብዓቶችን ጠይቆ ማሟላት፣ በመንግስት ንብረት አያያዝ ደንብ መሰረት መጠቀም፣
- በየወሩ በጤና ጣቢያ በሚደረገው የስራ ግምገማ ላይ በመገኘት በፓኬጆች አፈፃፀም የሚስተዋሉ የአመለካከት፣የክህሎትና የግብዓት ማነቆዎችን በመለየት መፍታት/እንዲፈቱ ማድረግ፤
- የ1ለ5 መሪዎችን ማሰልጠን፣ መከታተል፣ መደገፍና ብቁ ሲሆኑ  በሞዴል ቤተሰብነት ማስመረቅ፣
- የ1ለ5 መሪዎች የሚከታተሏቸውን ቤተሰቦች መከታተልና መደገፍ ብቁ ሲሆኑ በሞዴል ቤተሰብነት ማስመረቅ

## 8.8 የልማት ቡድን ተግባርና ኃላፊነት

**ቁልፍ ተግባር**

- በልማት ቡዱኑ ውስጥ ያሉ እማ/አባዎራዎች  የሚመለከታቸውን የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን ሙሉ በሙሉ እንዲተገብሩ ማድረግና ሌሎች የጤና ልማት ስራዎችን መስራት፣

DRAFT

**አበይት ተግባራት**

- በስሩ ያሉ ሁሉም ቤተሰቦች በ1ለ5 እንዲተሳሰሩ ማድረግ፤
- የልማት ቡድኑን አጠቃላይ ጤናና ጤና ነክ መረጃዎችን መሰብሰብ፤መተንተንና ማጠናቀር፣
- የቀበሌውን የጤና ዕቅድ መነሻ በማድረግ የልማት ቡድኑን ዕቅድ ማዘጋጀት፣በ1ለ5ና በቤተሰብ ደረጃ መከፋፈሉን ማረጋገጥና ተፈፃሚነቱን መከታተል፣
- ቢያንስ በየሁለት ሳምንቱ በመገናኘት የ1ለ5 ትስስሮችን መሰብሰብ፣መከታተል፣መደገፍና መገምገም፤
- የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ ማቅረብ፤

## 8.9 የ1ለ5 ትስስር ተግባርና ኃላፊነት

**ቁልፍ ተግባር**

- የልማት ቡድኑን የጤና ዕቅድ መነሻ በማድረግ የ1ለ5 ትስስር ዕቅድ ማዘጋጀት፣በዚሁ መሰረት በትስስሩ ያሉ ቤተሰቦች እንዲያቅዱ በማድረግና በመደገፍ ተፈፃሚነቱን መከታተል፣
- በ1ለ5 ትስስር ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች የሚመለከታቸውን የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን ሙሉ በሙሉ እንዲተገብሩ መደጋገፍ፣
- የትስስሩን አጠቃላይ ጤናና ጤና ነክ መረጃዎችን አጠናቅሮ መያዝ፣
- ቢያንስ በየሳምንቱ በመገናኘት የትስስሩ አባላትን የፓኬጆች አፈጻጸም መገምገምና መደጋገፍ እንዲሁም በየወሩ አፈፃፀማቸውን ደረጃ መስጠት፣
- የትስስሩን አባላት በማስተባበር በትስስሩ፣ በልማት ቡድኑና በቀበሌው የሚካሄዱ የጤና ልማት ሥራዎችን መስራት፣
- የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለልማት ቡድን ማቅረብ፣

## 8.10 የቤተሰብ ተግባርና ኃላፊነት

- የቤተሰቡን የጤና ዕቅድ ያዘጋጃል፤
- በ1ለ5 የትስስር መሪ የሚሰጠውን የክህሎት ሥልጠና በመከታተል በቤቱና በቤተሰቡ ይተገብራል፤ሌሎች ቤተሰቦችንም ይደግፋል፤
- በቋሚነት በ1ለ5 ትስስር፣በልማት ቡድንና በቀበሌ ውይይት ላይ ይሳተፋል፤
- በቀበሌው የሚካሄዱ የጤና ልማት ስራዎችን ይሰራል፤

DRAFT

## 8.11 የት/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

**ቁልፍ ተግባር**

- በትምህርት ቤት ሊተገበሩ የሚችሉ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ፓኬጆችን መተግበርና ለፕሮግራሙ ስኬታማነት ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ጋር መስራት፣

**አበይት ተግባራት**

- በትምህርት ቤት የጤና ክበብ በማቋቋም የጤና ትምህርት መስጠትና በሕብረተሰቡ የሚተገበሩ የጤና ልማት ሥራዎችን መደገፍ፣
- መደበኛውን የትምህርት ሂደት በማያስተጓጉል መልኩ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በሳምንት የተወሰነ ሰዓት በትምህርት ቤት ስለጤና አጠባበቅ ትምህርት የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- የተለያዩ የጠየና ተግባራትን የሚያመለክቱ ሰርቶ ማሳያዎችን በት/ቤት በማዘጋጀት (መፀዳጃ ቤት፣የእጅ መታጠቢያ፣የቆሻሻ ጉድጓድ፣ወዘተ.) እንዲጠቀሙ በማድረግ የተማሪዎችን ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ፣

## 8.12 የሴቶች አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት

**ቁልፍ ተግባር**

- በጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ሂደት በግንባር ቀደምነት መንቀሳቀስ፣

**አበይት ተግባራት**

- አባላቶቻቸውን በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ሞዴል እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ለጤና ልማት ቡድንና ለ1ለ5 ትስስር ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣
- በየደረጃው ካሉ የጤናው ሴክተር አካላት ጋር ተባብሮ መስራት፣
- በዕቅድ ዝግጅት አተገባበርና ግምገማ ላይ መሳተፍ፣

## 8.13 የአጋር ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት

- ከፌዴራል ጀምሮ እስከ የመጀመሪያ የጤና ክብካቤ አሀድ ባሉ የጤና መዋቅሮች ፍላጎት መሰረት ለፕሮግራሙ መሳካት አስፈላጊውን ሁሉን አቀፍ ድጋፍ መስጠት፣

***በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትግበራና በጤና ልማት ሰራዊት ግንባታ ሂደት የሚከተሉት ተግባራት የተከለከሉ ናቸው።***

- በቀበሌ ደረጃ ከ1ለ5 አደረጃጀት ማሰልጠን እንዲሁም ሌሎች በጎ ፈቃደኛ የጤና መልዕክተኞችን ማሰልጠንና መጠቀም፣

DRAFT

- ለልማት ቡድንና ለ1ለ5 መሪዎች እንዲሁም ለህብረተሰቡ በቀበሌ ደረጃ ለሚደረጉ የጤና ልማት ስራዎች ማንኛውንም አይነት ጥቅማጥቅም መስጠት፣
- የጤና ጥበቃ ሚኒስተር ከአጋሮች ጋር በመሆን ካወጣው የተቀናጀ የጤና ኤክስቴንሽን ማሰልጠኛ ማቴሪያል ውጪ ስልጠና መስጠት፣
- በየደረጃው ካለ የጤና መዋቅር ጋር ሳይቀናጁ አጋሮች ከጤና ኬላ በታች ወርደው መስራት፣

# 9. የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ ፕራክቲሽነሮች ዝውውር እና የአመት እረፍት

## 9.1 የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ ፕራክቲሽነሮች ዝውውር

የዝውውር፣የመልቀቂና ልዩ ልዩ እረፍት ፈቃድ በተመለከተ ግልፅ መመሪያ ባለመኖሩ በርካታ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከስራው ጫና ጋር በማወዳደር ለመስራት ፍላጎታቸው እንደቀነሰ እና ስራውን በጥራት ለማከናወን እንደ ችግር ታይቷል። ዝውውሩ የሚፈፀምባቸው ደረጃዎች ከቀበሌ ወደ ቀበሌ፣ ወረዳ ወደ ወረዳ እንዲሁም ከዞን ወደ ዞን ሊሆን ይችላል። የዝውውር ማወዳደሪያ መስፈርት በዋናነት በስራ አፈፃጸም ውጤታቸው ሊሆን ይገባል ።

***የዝውውር ማወዳደሪያ መስፈርቶች***

- ቢያንስ በየሁለት አመቱ በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ቀበሌዎችን
    - ባላቸው የስራ አመችነት፣
    - የገጠር መሰረተ ልማት መስፋፋት እና
    - የአየር ንብረት ሁኔታ በመለየት በቅደም ተከተል ደረጃቸውን ማውጣት
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራቸቲሽነሮች ከሚሰሩበት ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ ለመዛወር በተመደቡበት ቀበሌ ቢያንስ 2 አመት ማገልገል ይኖርባቸዋል፡
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራቸቲሽነሮች የሚወዳደሩበት መስፈርት በዋናነት በስራ አፈፃፀም ውጤታቸው መሰረት ነው።
- በወረዳው ውስጥ ከቀበሌ ቀበሌ ዝውውር ማድረግ ሲታሰብ በዋናነት ስድስት (6) መሰረታዊ ነገሮችን በመጠቀም የተሸለ ውጤት ያስመዘገቡ የተሸለ የስራ ቦታ ለሚገባቸው የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራቸቲሽነሮች መስጠት ያስፈልጋል። በዚህ መሰረት

  1. የሞዴል ቤተሰብ ምረቃ አፈፃፀም --------------------80%

2. ለስራ ቦታ ቀበሌዎች የሚሰጥ ነጥብ ------------------------8%
3. የአገልግሎት ዘመን/አመት --------------------------------------2%
4. የምታገለግለው ህዝብ/የቤተሰብ ኃላፊ ብዛት-------------------2%
5. ለትዳር የሚሰጥ ነጥብ -----------------------------------------3%
6. በቀበሌው ሊቀመንበር/ስራ አስኪያጅ የሚሰጥ ነጥብ --------5%

በነዚህ ማወዳደሪያ ነጥቦች እኩል ከመጡ. ቅድሚያ ለባለትዳር ይሰጣል፣በዚህም እኩል ከሆኑ በእያንዳንዱ ፓኬጅ አፈፃፀም ውጤት ይወዳደራሉ፡፡ እነርሱም፡-

1. የክትባት ማለትም የፔንታቫለንት3 /የሚዝልስ/ ሽፋን
2. የቅድመ ወሊድ፣የወሊድና የድህረ ወሊድ አገልግሎት ሽፋን
3. የ ቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ሽፋን
4. የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም ሽፋን በመውሰድ እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡

- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራቸቲሽነሮች በአዲስ ቅጥር ወይም በዝውውር ከሌላ ወረዳ/ዞን ዝውውሩ ከተሰራ/ከተጠናቀቀ በኋላ ከመጡ/ጣች በወረዳው ውስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች በጊዜያዊነት ተመድባ/በው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ በሚቀጥለው ዝውውር ባላቸውን አገልግሎትና የስራ ውጤት መሰረት ወደ ሚመጥናቸው ቦታ ይመደባሉ፡፡
- ዝውውር የሚፈልጉ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ባለሙያዎች የሚፈልጉትን ቀበሌ በደረጃ ከ1ኛ እስከ 3ተኛ በመዘርዘር ለዚሁ አላማ በተዘጋጀው የዝውውር መጠየቂያ ፎርም ሞልተው በወቅቱ ለወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን ለዝውውር የጠየቋቸውን ቀበሌዎች በስራ ውጤታቸው መሰረት ማግኘት የማይችሉ ከሆነ በውጤታቸው መሰረት የሚቀጥለውን ቀበሌ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
- በመመዘኛው መሰረት የተሸለ ቀበሌ ተመድበው ዝውውር የማይፈልጉ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ፕራቸቲሽነሮች ካሉበት ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ ለመዛወር ባይፈለጉ ወይም የዝውውር ፎርም ባይሞሉም የወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በየአመቱ በሚያወጣው የስራ አፈፃፀም ውጤቷ ዝቅተኛ ከሆነ በውጤቷ መሰረት ወደሚመጥናት ቀበሌ እንድትዛወር ይደረጋል፡፡
- ዞን እና ከወረዳ ወረዳ ለሚደረግ ዝውውር የተቀባይና ላኪ ስምምነት መኖሩን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

DRAFT

*የዝውውር አይነቶች*

*1.በጋብቻ*

ከላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባልና ሚስት የዝውውር ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት ጋብቻ የመሠረቱ መሆኑን የሚያረጋግጥ ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ይህም በፋይላቸው ተያይዞ መገኘት ይኖርበታል፡፡ የዝውውሩ ሁኔታ ከወረዳ/ዞን ወደ ወረዳ/ዞን ከሆነ በሁለቱ ወረዳዎች/ዞኖች እውቅናና ስምምነት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

*2.በጤና ችግር የሚፈፀም ዝውውር*

የጤና ኤክስቴሽን ሰራተኞች/ፕራቾቲሽነሮች ከሚሠሩበት ቦታ የጤና መታወክ ችግር ሲያጋጥማቸውና ባሉበት ቦታ የህክምና አገልግሎት ማግኘት እንደማይችሉ በሐኪሞች ቦርድ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ ከቻሉ ህክምና ሊገኙ በሚችሉበት አቅራቢያ ቦታ ክፍት ቦታ ሲኖር ዝውውሩ ይታይላቸዋል፡፡

*3.የርስ በርስ ዝውውር*

ከላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ኤክስቴሽን ሰራተኞች/ፕራቾቲሽነሮች የርስ በርስ ዝውውር ማድረግ ከፈለጉ የመደበኛውን የዝውውር ጊዜ ሳይጠብቅ ሁለቱም 80% በላይ የሚሆነውን ቤተሰብ በሞዴልነት ካስመረቁ ዝውውሩ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡ የዝውውሩ ሁኔታ ከወረዳ/ዞን ወደ ወረዳ/ዞን ከሆነ በሁለቱ ወረዳዎች/ዞኖች እውቅናና ስምምነት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## 9.2 የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች/ ፕራክቲሽነሮች የአመት እረፍት በተመለከተ

1. የጤና ኤክስቴንሽን ሥራዎች ዓመቱን በሙሉ የሚካሄዱ ቢሆንም በተነፃፃሪ በውሉገብ እና ቤት ለቤት የሚሰጠው አገልግሎቶች ውስን በሚሆንበት የክረምት ወቅት ሊሆን ይገባል፡፡ ክረምቱ ቀድሞና ዘግይቶ የሚገባባቸው እንደየ አካባቢው ሊለያይ ቢችልም በአብዛኛው ግን በሀምሌና በነሃሴ ይሆናል፡፡

DRAFT

2. በጤና ኬላ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶች እንዳይቋረጡ በክላስተር ጤና ጣቢያው በኩል ተራ ወጥቶላቸው በኘሮግራም ይሆናል፡፡ ፈቃዱ የሚሰጠበት ጊዜም ለየብቻ በየተራ ይሆናል፡፡

## 10. ተከታታይነት ያለው የስራ ላይና የሙያ ማሻሻያ ስልጠና

የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን በብቃት እንዲፈፅሙና ለህብረተሰቡ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ተከታታይነት ያለው የስራ ላይ ስልጠናና የሙያ ማሻሻያ ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡  ፓኬጆችን ከመፈፀም አንፃር የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ያለባቸውን የክህሎት ክፍተት በመለየት በየሁለት አመት  ጤና ጥበቃ ሚ/ር  በሚያዘጋጀው የማሰልጠኛ ማኑዋሎችን  በመጠቀም በተቀናጀ መልኩ ስልጠና መስጠት ይገባል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ሲከናወኑ የነበሩትን አገልግሎቶች ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገርና በጤና ኬላ ደረጃ የሚሰጠው የጤና አገልግሎት በመጠንም ሆነ በይዘት ለማሻሻል የሰራተኞችን እውቀትና ክህሎት በተጨማሪ ስልጠና በማሰደግ፣ የተሸለ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

## 11.የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የድጋፍና ክትትል ማዕቀፍ

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙንና የጤና ልማት ሰራዊት ግንባታውን ገቢራዊነት ለማረጋገጥ በየደረጃው የተጠናከረ ድጋፍና ክትተትል ሊደረግ ይገባል፡፡ በየደረጃው ለሚደረገው የድጋፍና ክትትል ስራዎች ሶስት ዋና ዋና የድጋፍና ክትትል አግባቦችን እንከተላለን፡- እነሱም መደበኛ የጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት፣ ድጋፋዊ ክትትልና ኢንስፔክስሽን እንዲሁም የአፈፃፀም ግምገማዎች ናቸው፡፡

### 11.1 መደበኛ የጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት (HMIS)

የጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት በሀገሪቱ በመተግበር ላይ ሲሆን በዚህም የሚገኘውን መረጃ ለውሳኔ አሰጣጥ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በየደረጃው የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ወደ ሚቀጥለው የጤና እርከን ከማስተላለፍ በተጨማሪ የተሰበሰበውን መረጃ በመጠቀም የውስጥ ግምገማ ማካሄድ፣ ማነቆዎችን መለየትና አስፈላጊውን የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

በዚህም መሰረት የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከቀበሌ ኮማንድ ፖስት ጋር በሚያደርጉት መደበኛ ስብሰባ በጤና ኬላ ደረጃ በጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት የሚሰበሰበውን ሪፖርት አጀንዳ በማድረግ መገምገምና የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡

DRAFT

በጤና ጣቢያ ደረጃ የጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓትን መሰረት በማድረግ በስሩ ከያዛቸው ጤና ኬላዎች ጋር በመሆን በየወሩ የአፈፃፀም ግምገማ ያካሂዳል፡፡ በግምገማውም ወቅት በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች አፈፃፀም የሚታዩ ማነቆዎችን በመለየት አስፈላጊ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፡፡

በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ደረጃ በየወሩ በጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት የሚሰበሰበው ሪፖርት መሰረት በማድረግ የፕሮግራሙን አፈፃፀም በመገምገም የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በዞን፣ በክልልና በፌዴራል ደረጃ በየወሩ በጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት ውስጥ ባሉ በተመረጡ[1] መለኪያዎች መሰረት የአፈፃፀም ግምገማ በማካሄድ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡

በወረዳ፣ በዞን፣ በክልልና በፌዴራል ያለው የኮማንድ ፖስት አደረጃጀትም በሚያካሂደው መደበኛ ስብሰባ ላይ በጤና መረጃ አስተዳደር ስርዓት ውስጥ ያሉ የተመረጡ መለኪያዎች በተጨማሪ በየወሩ ሪፖርት የሚደረገውን በ1ለ5 እና በልማት ቡድን የተሰሩ ስራዎችን መሰረት በማድረግ አፈፃፀማቸውን ይገመግማል፤ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡

## 11.2 ድጋፋዊ ክትትልና ኢንስፔክሽን

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የታለመለትን ግብ ለማሳካት በየደረጃው የተጠናከረና ቀጣይነት ያለው ድጋፍና ክትትል ማካሄድ ወሳኝ ነው፡፡ በቀበሌ ደረጃ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ከልማት ቡድኖችና ከ1ለ5 ትስስር መሪዎች ጋር ቢያንስ በየሁለት ሳምንቱ በመገናኘት በፓኬጆች አፈፃፀም በተለይም ትኩረት በሚሰጣቸው የጤና አገልግሎቶች (በጤና ተቋማት የሚሰጥ የወሊድ አገልግሎት፣ በእርግዝና ወቅት የኤች አይ ቪ ኤድስ ምርመራ፣ የክትባት አገልግሎት፣ የወባ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ስራዎች እንዲሁም እንደ የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ትኩረት በሚሰጣቸው የጤና አገልግሎቶች) ላይ በመወያየት አፈፃፀማቸውን ይገመግማሉ፤ በዚህ ሂደትም የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን በአመለካከት፣ በክህሎትና በግብዓት በመተንተን መፍትሔዎችን ያስቀምጣሉ፡፡

በጤና ጣቢያ ደረጃ የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በስራቸው ያሉ ጤና ኬላዎችን በመከፋፈል በየሳምንቱ በቼክሊስት በመታገዝ ይደግፋሉ፡፡ የሚካሄዱ ድጋፍና ክትትሎችም በፓኬጆች አፈፃፀም የሚታዩ የአመለካከት፣ የክህሎትና የግብዓት ማነቆዎችን የሚፈቱ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ ዳይሬክተርም የድጋፍና ክትትል ስራውን በበላይነት ያስተባብራል፤ ይመራል፡፡

በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ደረጃ ቢያንስ በየወሩ ወጥ የሆነ ቼክሊስት በመጠቀም ለጤና ጣቢያዎችና ጤና ኬላዎች ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፡፡ በድጋፍና ክትትሉ ለተለዩት ማነቆዎችም አስፈላጊውን የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፡፡

[1] የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት፣በሰለጠነ ባለሙያ የሚሰጥ የወሊድ አገልግሎት፣PMTCT፣የክትባት አገልግሎት፣የመፀዳጃ ቤት ግንባታና አጠቃቀም፣ወባን ለመከላከል የአከባቢ ቁጥጥር ስራዎች፣የቲቢ ህሙማን ልየታ

DRAFT

የዞን ጤና መምሪያ፣ የክልል ጤና ቢሮና ፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር በመቀናጀት ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ ወጥ የሆነ ቼክሊስት በመጠቀም የዞኖችን፣ የወረዳዎችን፣ የጤና ጣቢያዎችንና የጤና ኬላዎችን በአፈፃፀም ደረጃቸው በመለየት ድጋፍና ክትትል ያደርጋሉ፡፡ ይህ በቅንጅት የሚደረገው ድጋፍና ክትትል በየደረጃው የተለዩ ማነቆዎችን ማን በባለቤትነት መፍታት እንደሚገባው ኃላፊነት ለመስጠት፣ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም ላይ ተመሳሳይ አረዳድ ለመያዝ እንዲሁም በሚደረጉ ድጋፍና ክትትሎች ባጭር ጊዜ ብዙ ዞኖችን፣ ወረዳዎችንና ጤና ተቋማትን ለመሸፈን ጠቀሜታው የላቀ ነው፡፡

በየደረጃው የሚደረግ ድጋፍና ክትትል ሶስቱን የድጋፍና ክትትል ማዕቀፎችን (ሪፖርት፣ ኢንስፔክሽንና ግብረመልስ) ተከትሎ ሊደረግ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት ድጋፍና ክትትል የሚያደርገው አካል ወደ መስክ ከመውጣቱ በፊት ድጋፍ ስለሚሰጠው አካል የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን በመገምገም ትኩረት መስጠት ያለበትን የጤና አገልግሎቶች መለየት፤ እስከ ቤተሰብ ድረስ በመውረድ ሪፖርት የተደረጉ ስራዎች ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥና ግኝቱን ለሚመለከተው ሁሉ ግብረመልስ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ በድጋፍና ክትትሉም ወቅት በየደረጃው ያሉ ማነቆዎችን ከመለየትና መፍትሔ ከማፈላለግ በተጨማሪ ምርጥ ተሞክሮዎችን የመቀመርና የማስፋት ስራ መሰራት ይኖርበታል፡፡

ከድጋፋዊ ጉብኝኘት ጎን ለጎን በየደረጃው ያለው አመራር ወደ ታች በመውረድ የተሰሩ ስራዎችና ሪፖርት የሚደረገውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኢንስፔክሽን ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም የቀበሌው አመራር በየሁለት ሳምንቱ እንዲሁም የወረዳ አመራሮች ቢያንስ በየወሩ በቀበሌ ደረጃ የተከናወኑ ተግባራትን ለማየት የኢንስፔክሽን ስራ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡

## 11.3 የአፈፃፀም ግምገማዎች

በየደረጃው የሚካሄዱ ግምገማዎች በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም ሂደት የተለዩ ማነቆዎችን ለመፍታት፣ እርስ በርስ ልምድ ለመለዋወጥ እንዲሁም የተሻለ አፈፃፀም ላስመዘገቡ አካላት እውቅናና ማበረታቻ ለመስጠት የምንጠቀምባቸው መድረኮች ሊሆኑ ይገባል፡፡ ስለሆነም በወረዳ ደረጃ በየሩብ ዓመቱ ጤና ኬላዎችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ የሴቶች አደረጃጀቶችንና በወረዳው ውስጥ የሚሰሩ አጋሮችን ያሳተፈ የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ ያካሂዳል፡፡ በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላላቸው አካላት እውቅናና ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

በዞን ደረጃም በየሩብ ዓመቱ በየደረጃው ያሉ አካላትንና አጋሮችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ በማዘጋጀት በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላላቸው አካላት እውቅናና ማበረታቻ ይሰጣሉ፡፡

በክልል ደረጃም በየግማሽ ዓመቱ በየደረጃው ያሉ አካላትንና አጋሮችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረክ በማዘጋጀት በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላላቸው አካላት እውቅናና ማበረታቻ ይሰጣሉ፡፡

በፌዴራል ደረጃ በየዓመቱ ሁሉንም ክልሎችና አጋር ድርጅቶችን ያሳተፈ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ይካሄዳል፡፡ በዚህም በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም የተሻለ ደረጃ ላላቸውና የላቀ አስተዋፅዖ ላበረከቱ አካላት እውቅናና ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

DRAFT

በየደረጃው የተቋቋመው ኮማንድ ፖስት ቼክ ሊስት በመጠቀም በተዋረድ ሁሉን አቀፍ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

በየደረጃው ከሚካሄዱ የአፈፃፀም ግምገማዎች በተጨማሪ በራስ ተነሳሽነትና በገለልተኛ አካላት በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈፃፀም ላይ ጥናቶችን በማስጠናትና በሌሎች አካላት የተደረጉ ጥናቶችን በመጠቀም በፕሮግራሙ ላይ ቀጣይነት ያለው የማሻሻያ ስራ ይሰራል፡፡

## 12. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አደረጃጀት፣

**የፕሮግራም አደረጃጀት**

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በማህበረሰብ ደረጃ ጤናን የማበልፀግና በሽታን የመከላከል እንዲሁም መሠረታዊ ህክምናን የሚሰጥ አገልግሎት ነው፡፡ የጤና ኬላ በሀገሪቱ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት የመጀመሪያ እርከን በሆነው በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ውስጥ ከጤና ጣቢያ ጋር ቅርብ ትስስር ያለው ሲሆን በቀበሌ ደረጃ የሚተገበር ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ጤና ጣቢያዎች የህብረተሰብን ብዛትን አስፋፈር መሰረት ተደርጎ ባለመገንባታቸው ምክንያት የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የስራ ሃላፊነት ለወረዳ  ተስጥቶ ነበር ምንም እንኳን ወረዳዎች በፕሮግራሙ ላይ ከማቀድ ጀምሮ እስከትግበራ ድረስ የመደገፍ መከታተልና መገምገም ቀጣይነት ያለው ስራ የሚያከናውኑ ቢሆንም ከአሁን በሀላ የጤና ኬላዎች ተጠሪነት ሙሉ በሙሉ ለጤና ጣቢያና ለቀበሌ አስተዳደር ይሆናል፡፡

- በጤና ኬላ በአማካይ ከሚመደቡ ሁለት የጤና ኤክስቴንሽን ፕራክቲሽነሮች/ሰራተኞች መሃከል የጤና ኬላ ሀላፊና የቀበሌ ካቢኔ አባል የምትሆነው በጤና ጣቢያውና በቀበሌ መስተዳድር የጋራ ውሳኔ ትመረጣለች

- ከጤና ጣቢያ ጀምሮ እስከ ፌዴራል ያሉ የጤና መዋቅር አመራሮች የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ቁልፍ ተግባር አድረገው ይመራሉ፡፡

DRAFT

## አባሪ 1. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ፓኬጅ ይዘቶች

**? ????? ? ? ?? ??? ? ???**

- ?????? ???? ? ? ? ??
- ?? ? ? ? ? ? ?? ??? ? ??
- ????? ??? ? ??
- ????? ? ??
- ??? ? ?? ? ??

**?. ???? ? ? ? ????? ???? ????**

- ??? ??? ? ????? ? ???? ? ? ??
- ??? ? ?.??.?/??? ? ????? ? ???? ? ???
- ?? ?? ?? ??? ? ????

**? . ?????? ???? ? ? ?? ??? ????**

- ??? ???? ?? ??? ? ??
- የጤናማ መኖሪያ ቤት አያያዝ ፓኬጅ
- ተባዮች፣ቆርጣሚዮችና ተናደፊዎች ቁጥጥር ፓኬጅ
- የመጸዳጃ ቤት አሠራር፣ አያያዝና አጠቃቀም ፓኬጅ
- የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ፓኬጅ
- የውሃ ንጽሕና አጠባበቅ ፓኬጅ
- የምግብ ንጽሕና አጠባበቅ ፓኬጅ

**? .?? ? ?? ??? ?? ???? ?????? ???? ???**

DRAFT

## አባሪ2. በጤና ኬላ ደረጃ ሊኖሩ የሚገባቸው መድኃኒቶችን የህክምና መገልገያ ቁሳቁሶች

- ፓራሲታሞል
- ኦ አር ኤስ
- ዴፖ
- ፒልስ
- ኮንደም
- ኢምፕላኖን
- ኳርተም
- ክሎሮኪዊን
- አይረን ፎሌት
- ፎሊክ አሲድ
- ቴትራሳይክሊን
- አሞክሳሲሊን
- ኮትሪሜክሳሶል
- ዚንክ ታብሌት
- አልቤንዳዞል
- ፕላምፕኔት
- ክትባት
- አር ዲ ቲ

DRAFT